## ደሜ መሰላሉ!



ተሰባ ዓመት በፊት ተዋርዶ የወጣው!
አማራን ሊበቀል ክልልን የሳለው፣
ፋሽሽት ሞሶሎኒ ለገሰን ደቀለው።

ዲቃላው ለባንዳ ለአቅመ-ተንኮል ሲደርስ፣
ጨልጥ አርጎ ጠጣው የፋሽሽትን መንፈስ።

የፋሽሽት መንፈስ ተሰቅሎ ሲያስጎራው፣
በአማራ መቃብር መንደር መስርት አለው።

በአማራ መቃብር መንደር ለመመስረት፣
መጋዣውን ገዛ የሚባል ታምራት።

ተመጋዣው መጥቶ በሱዳን ታጅቦ፣
የምዕራብ ሰዎችም መብራት እያበሩ፣
አራት ኪሎ ገባ እርኩስ መንፈስ ይዞ።

መጋዣው ስኳሩን ልሶ በምላሱ፣
ትከሻው ሲሰፋ ሲወፍር ደንደሱ፣
ወህኒ ወረወረው ጌታው በመስጋቱ።

ታምራት መጋዣው ተጋጡ ሲታሰር፣
አህያው ተተካ አዲሱ የሚባል።

አህያው ተገጥቦ ጡረታ ሲወጣ፣
ደመቀ የሚባል መሰላል ተተካ።

ደሜ መሰላሉ የሰው ግዑዝ ነገር፣
ቢረግጡት ቢረምዱት ሲጢጥ እንኳን አይል።

መልምሎና ጠርቦ መሰላል የሰራው፣
መሰላሉ ደሜ ጭነት እንዳይከብደው፣
እንደ አሳማ አብልቶ ደንደሳም አረገው።

በዚህ መሰላል ላይ እየተራመደ፣
በመላ አገሪቱ አማራን አረደ።

ደም በነካ ጫማው ደጋግሞ ሲረግጠው፣
ደሜ መሰላሉ ይባስ አደነቀው።

ደጋግሞ ረጋጩን እግዜር ሲያነሳለት፣
አሽከሩ ደሳለኝ ተፈናጠጠበት።

በጥንግር እያዬ ደሴ ሲወጣበት፣
ዶሮ ወጡን ይዞ ሲመላለስበት፣
ደሜ መሰላሉ አላለውም ስግጥጥ።

በፈረንጆች ትዕዛዝ ደሴ በቃህ ሲባል፣
የኖህ ቁራ መስሎ የተሰበረ እግር፣
የኳሊት ወረደ በደሜ መሰላል።

ለገሰን መልምሎ ወንበር የሰቀለው፣
ኸርማን ኮን ፓስተሩን ለጠቅላይ ሲሾመው፣
ደሜ መሰላሉ “ና ውጣብኝ!” አለው።

ደሜ መሰላሉ ደም የማይከረፋው፣
ዛሬም እንደገና አማራን አስፈጀው።

ደሜ መሰላሉ ወገቡን አያመው፣
እንደተገተረ ዛሬም አለ ይኸው!

ተምክትል ጉድጓድ እግሩ የበቀለው፣
ደሜ መሰላሉ ጭነት የማይከብደው፣
ተነግ ወዲያ ደሞ ማን ይፈናጠጠው?

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ታህሳስ ሁለት ሺ አስራ ሁለት  ዓ.ም.